Amharic

ሃይማኖት እና ሃይማኖታዊ
መስተንግዶ
የሚመለከት መመሪያ

## ዳራ (Background):

በ2019-2020 የትምህርት ዘመን፣ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የሲያትል የትምህርት ማህበር የተማሪ እና የስራ የቀን መቁጠሪያዎችን ለማዘጋጀት ከሀይማኖታዊ እና ባህላዊ አከባበር እና ልምምዶች ጋር የተያያዙ ፍትሃዊነትን ለመፍታት እና አካታች ጉዳዮችን ለመገምገም የጋራ የስራ ቡድን ፈጥረዋል።ይህ የስራ ቡድን በማህበረሰባችን ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያላቸውን ቀናት ግምት ውስጥ በማስገባት፣ከዚህ በታች ባለው የስምምነት የቀን መቁጠሪያ ቀመር (አስፈላጊ ቀናት) በመጠቀም የቀን መቁጠሪያ እንዲያዘጋጅ ታስቦ የተቋቋመ ነው።የዚህ የቀን አቆጣጠር ግብ ትምህርት ቤቶች/መምህራን አስፈላጊ ዝግጅቶች፣ፈተና እና የፈተና ቀናት ሲያቅዱ ለመርዳት፣ የተለያዩ ሃይማኖታዊ በዓላትን እና አከባበርን በተወሰነ መልኩ ለማሳየት ነው።

ሁሉንም ሃይማኖታዊ/ባህላዊ አከባበር ለማስተናገድ የትምህርት አመት ቀናትን መቀየር ባንችልም ተማሪዎች ሃይማኖታዊ ልማዶቻቸውን ለማክበር ከትምህርት እና አስፈላጊ የትምህርት ቤት ዝግጅቶች ሊቀሩ እንደሚችሉ ግልፅ ነው።የትምህርት ቤታችን ዲስትሪክት በጣም ትልቅ ስለሆነ ማህበረሰቦቻችን በብዝሃነታቸው ይለያያሉ።በዚህም ምክንያት፣ዲስትሪክቱ እያንዳንዱን ትምህርት ቤት ማህበረሰቡን እንደሚያቅ ይገነዘባል እና ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤት ማህበረሰብ ውስጥ በሚከናወኑ የሃይማኖታዊ/ባህላዊ በዓላት ቀናት ላይ አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት ቤቶች መርሃ ግብሮችን ማስቀረት ካልቻሉ ለተማሪዎች ሊሰጡ የሚችሉትን መስተንግዶ እና ድጋፎች እንዲያጤኑ ይጠይቃል።በተጨማሪም፣የዋሽንግተን ስቴት ህግ እና የዲስትሪክቱ ዋና ሃላፊ አሰራር 3121SP፣ተማሪዎች ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ በዓልን ለማክበር ከትምህርት መቅረት ምክንያታዊ እንደሆነ ይደነግጋል።

ይህ መመሪያ ከህዝባዊ ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ጽሕፈት ቤት በሚሰጠው መመሪያ ላይ የተመሠረተ ነው።

## አስፈላጊ ቀኖች:

*ከዚህ በታች ያሉት ቀናት የህብረቱ የድርድር ስምምነት (Collective Bargaining Agreement (CBA)) አካል ናቸው።*

- **የትምህርት መጀመሪያ ቀን**
  - የመስከረም ወር የመጀመሪያው ረቡዕ
- **የስቴት የአገልግሎት(In-Service)ቀን**
  - በስቴቱ እንደታወቀው (በተለምዶ በጥቅምት ወር ሁለተኛ አርብ)
- **የክረምት እረፍት**
  - ቢያንስ አስር የስራ ቀናት፣ከአዲሱ አመት የመጀመርያ ቀን በኋላ ያበቃል።የአዲስ ዓመት የመጀመርያ ቀን ሰኞ ከዋለ ወይም ከተከበረ፣ተማሪዎች በሚቀጥለው ቀን (ማክሰኞ) ወደ ትምህርት ቤት ይመለሳሉ።
- **የክረምት አጋማሽ እረፍት**
  - የፕሬዚዳንት ቀን እና የሚቀጥሉት አራት የስራ ቀናት
- **የፀደይ እረፍት**
  - የሚያዝያ ወር ሁለተኛ ሰኞ ጀምሮ ለአምስት ቀና
- **የበረዶ ማካካሻ ቀናት(Snow Make-Up Days)**
  - በሴሚስተሮች መካከል ያለውን ቀን እና በሰኔ ወር ከመጨረሻው የትምህርት ቀን በኋላ ባሉት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናት ጨምሮ ቢያንስ ሶስት የበረዶ ማካካሻ ቀናት መርሐግብር ተይዘላቸዋል።አስፈላጊ ከሆነ በሰኔ ወር ተጨማሪ የበረዶ ማካካሻ ቀናት ሊጨመሩ ይችላሉ።
- **በዓላት**
  - የሰራተኛ ቀን (ትምህርት በመስከረም ወር ከዚህ ቀን በፊት ሲጀምር)
  - የአርበኞች ቀን (ህዳር)
  - የምስጋና ቀን (ህዳር)
  - ከምስጋና ቀን ማግስት (ህዳር)
  - የማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር ቀን (ጥር)
  - የፕሬዝዳንት ቀን (የካቲት)

- ○ መታሰቢያ ቀን (ግንቦት)
- ○ Juneteenth(ሰኔ)

- **የኮንትራት ቀናት (Contractual Days)**
  - ○ የኮንትራት( የስምምነት) ቀናት (Contractual Days) ።ከትምህርት መጀመሪያ በፊት ያሉት አራት የስራ ቀናት፣ከሰራተኛ ቀን በፊት ካለው አርብ በስተቀር
- **ኮንፈረንሶች**
  - ○ ከምስጋና ቀን በፊት ሰስት ተከታታይ ቀናት

## የተማሪ መቅረት

*ፖሊሲ 3121 ይመልከቱ፡ [አቴንዳንስ]*

ምንም እንኳን ተማሪዎች ሁሉጊዜ በትምህርት መገኘት አስፈላጊ ቢሆንም፣ፖሊሲ 3121 በሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ዓላማዎች ምክንያት ከትምህርት መቅረት ምክንያታዊ እንደሆነ ይደነግጋል።ከስር ያለውን ይመልከቱ።

> *ፖሊሲ 3121: በመደበኛነት በትምርሀት ቤት መገኘት የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ያለውን የእያንዳንዱ ተማሪ የትምህርት ልቀት ተልእኮ ለማሳካት አስፈላጊ ነው።ያለምክንያት መቅረትን እና ማርፈድን ለመታገል፣የዕለታዊ አቴንዳንስ እንቅፋቶችን ለማስወገድ፣ሁሉም የሲያትል ህዝባዊ ት/ቤቶች በዘር፣በባህል እና በእድሜ ተስማሚ የሆኑ ትምህርቶች፣ጣልቃገብነቶች እና ድጋፎች ለማቅረብ ቆርጦ ተነስቷል።*

ፖሊሲ 3121 በሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ዓላማዎች ምክንያት ከትምህርት መቅረት ምክንያታዊ

እንደሆነ ይደነግጋል።

<u>የዋና ሃላፊ አሰራር 3121SP VIII.B.a.3. and 12.</u> <u>ስቴት(Superintendent Procedure 3121SP VIII.B.a.3. and 12. State) :</u>

*a) B . ምክንያታዊ መቅረት(Excused Absences ) በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ መቅረት በ RCW 28A.225.010 ወይም WAC 392-401-020 መሠረት ይቅርታ መደረግ አለበት፡*

> *3. ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ በዓል ለማክበር ወይም በሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ትምህርት ለመሳተፍ ጨምሮ ለሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ዓላማ (WAC 392-401-020)፤እና*
>
> *12. በእምነት ወይም ጎሊና ወይም በሃይማኖት ቤተ እምነት፣ቤተ ክርስቲያን ወይም የሃይማኖት ድርጅት ሥር ለሚደረግ የተደራጀ ተግባር ምክንያት በትምህርት ዓመቱ እስከ ሁለት ቀን ድረስ (RCW 28A.225.010(1)(e)) ።*

*ፖሊሲ [Policy 3121]/[3121SP] ሙሉ በሙሉ ይመልከቱ፣ሆኖም ግን የሚከተሉትን ያቀርባል:*

- ○ የትምህርት ቤቱ ርእሰመምህር (ወይም ተወካይ) መቅረቱ ምክንያታዊ መሆኑን ለመወሰን ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን የማየት ስልጣን አለው።
- ○ መቅረቱ ምክንያታዊ ከሆነ፣ተማሪው ያመለጡትን የትምህርት ስራዎች በሙሉ ከክፍል ውጪ በሚሞች ሁኔታ እና የክፍል መምህር በመቻቸው የጊዜ ገደብ እንዲወስድ ይፈቀድለታል።ነገር ግን፣በመደበኛ ክፍል ያመለጡ ተግባራትን ለማካካስ የሚሰጡ ከትምህርት ግቦች ጋር የሚስማሙ አማራጮች በሚሞች ሁኔታ ካልቀረቡ፣ተማሪው በክፍል ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትን ማከናወን ባለመቻሉ የተማሪው ውጤት ሊጎዳ ይችላል።
- ○ ምክንያታዊ መቅረት በወላጅ/አሳዳጊ ወይም አዋቂ፣ራሱ የቻለ ወይም በተገቢው ዕድሜ ላይ ያለ ተማሪ፣ወይም ስለ መቅረት ኃላፊነት ያለው የትምህርት ቤት ባለስልጣን ይረጋገጣል።በኦንላይን ለሚሰጥ ወይም ተማሪዎች በዲስትሪክቱ ውስጥ በአካል በመገኘት ለሚወስዱት ኮርስ አቴንዳንስ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ የሚወሰድ ከሆነ፣መቅረቱ ምክንያታዊ መሆኑን በወላጅ/አሳዳጊ ወይም አዋቂ፣ራሱ የቻለ ወይም በተገቢው ዕድሜ ላይ ያለ ተማሪ፣

እስከሚረጋገጥ ድረስ ምክንያታዊ አይሆንም።በማንኛውም እድሜ ላይ ያለ ተማሪ ከቤተሰብ እቅድ ወይም ፅንስ ማስወረድ ጋር የተገናኘ የጤና እንክብካቤ ከሆነ ተማሪው፣ዲስትሪክቱ መረጃውን በሚስጥር እንዲይዝ ሊጠይቅ ይችላል።አሥራ ሦስት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተማሪዎች ስለ አደንዛዥ ዕፅ፣አልኮል ወይም የአእምሮ ጤና ሕክምና መረጃ በሚስጥር የመጠበቅ መብት አላቸው።አሥራ አራት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተማሪዎች ኤችአይቪ እና በፆታዊ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን በተመለከተ ተመሳሳይ ሚስጥራዊ መብቶች አሏቸው።

## የተማሪዎች ሃይማኖታዊ መስተንግዶ(Accommodations)

*ፖሊሲ 2340 ይመልከቱ: Religion and Religious Accommodation*

*ፖሊሲ 2340 በተጨማሪም ተማሪዎች ሃይማኖታዊ በዓልን ለማክበር ከትምህርታቸው ቢቀሩ ምክንያታዎ መሆኑን ይገልጻል።*

*ፖሊሲ 2340: ተማሪው ሃይማኖታዊ በዓልን ለማክበር ከትምህርት ለመቅረት የፍቃድ ጥያቄ ከወላጅ/አሳዳጊ ከቀረበ፣ተማሪው ፍቃድ ይሰጠዋል።በሃይማኖታዊ ምክንያት ከትምህርት የሚቀሩ ተማሪዎች በሌሉበት ያመለጣቸውን ማንኛውንም ሥራ፣ ተግባር ወይም ፈተና ለማካካስ እድሉ ሊኖራቸው ይገባል።*

*ፖሊሲ 2340SP: ትምህርት ቤቱ ተገቢውን ዝግጅት እና የጊዜ ሰሌዳ ማስተካከያ እንዲያደርግ፣የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ለተማሪው ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር የጽሁፍ ጥያቄ አስቀድሞ ማቅረብ አለበት።*

የጽሁፍ ጥያቄው የሚከተሉትን መግለጽ አለበት።

1. የሚጠየቀውን ግልፅ መስተንግዶ(accommodation)
2. መስተንግዶው(accommodation) ለምን እንዳስፈለገ
3. የመስተንግደው(accommodation) ጊዜ፣ቆይታ እና ድግግሞሽ

## የፈተና ቀናት - ሁሉም የፈተና ቀናት በፈተና ኤጀንሲዎች እስኪረጋገጡ ድረስ ጊዜያዊ ናቸው።

የትምህርት ቤት ሰራተኞች እነዚህን የፈተና ጊዜዎች እና አሰጣጣቸው የትምህርት ቤታቸው ማህበረሰቦች ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ አከባበር ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

**የ 2023-24 የስቴት የፈተና ጊዜ**

- **WaKIDS:** መረጃው እስከ ህዳር 15, 2023 ድረስ በ TS Gold ይገባል
- **WIDA Annual:** ከጥር 29 እስከ መጋቢት 22 ,2024
- **WA-AIM:** ከጥር 29 እስከ ግንቦት 3, 2024
- **SBA ELA & Math:** ከመጋቢት 4 እስከ ሰኔ 7፣2024
- **WCAS Science:** ከሚያዚያ 8 እስከ ሰኔ 7፣2024

SAT/PSAT በጥቅምት ወር፣AP ደግሞ በግንቦት ወር ይሰጣል።

## ሃይማኖት እና ሃይማኖታዊ መስተንግዶ(Accommodations)፣2023-2024

የዚህ ዓላማ በተማሪዎቻችን እና በቤተሰቦቻችን መካከል ስላለው የብዝሃነት ዓይነቶች እና ተማሪዎች በሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ምክንያት በትምህርት ቤት ሊገኙ ወይም ላይገኙ የሚችሉባቸውን ቀናት እንዲሁም ተማሪዎች ሊጾሙ ስለሚችሉባቸው ቀናት ግንዛቤን ለማስፋት ነው።እንዲሁም ቀኑ ሊቀየር በማይችልበት ጊዜ ትምህርታዊ ተግባራትን በተሻሉ ጊዜዎች ለመስጠት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፣ተማሪዎች ፀሃይ ስትጠልቅ በሚመገቡበት ወቅት በጠዋት ጊዜ ፈተና መስጠት።

ከዚህ በታች ያለው የቀን መቁጠሪያ ዓላማ በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ ባሉ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ስለሚኖሩ ሃይማኖታዊ በዓላት ግንዛቤን ለማሳደግ ለመርዳት ነው።

**ይህ የቀን መቁጠሪያ የዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የበዓላት እና የሃይማኖታዊ አከባበር በመመስረት የህዝብ ትምህርት የበላይ**

Amharic

**ተቆጣጣሪ ቢሮ ያቀረበው ነው።**

የሕዝብ ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ጽሕፈት ቤት ዲስትሪክቶች በዋና ዋና ሃይማኖታዊ በዓላት ላይ ጉልህ የሆኑ የት/ቤት ዝግጅቶችን እንዳያዘጋጁ ያበረታታል።በዋና ዋና ሃይማኖታዊ በዓላት ዙሪያ ቀድመው የሚያቅዱ ትምህርት ቤቶች፣ሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ትርጉም ያለው አካላት መሆናቸውን እና ሃይማኖታዊ ባህሎቻቸው አስፈላጊ መሆኑን መልእክት ያስተላልፋል። [1]

*ማሳሰብያ:*
*የ ሁሉምJewish, Islamic, እና Bahá'í በዓላት ከበዓሉ መጀመሪያው ቀን በፊት ያለው ምሽት ፀሃይ ስትጠልቅ ይጀምራሉ።*
*+ እነዚህ በዓላት (ወይም በበዓላቶች ውስጥ ያሉ ቀናቶች) የማይሰሩ (የሚከበሩ) ቀናት ተብለው ተሰይሟል።*
*# ከእነዚህ ቀናት ውስጥ አንዳንዶቹ በቀን መቁጠሪያ ላይ የተቀመጡ አይደሉም ነገር ግን በጨረቃ እይታ ላይ የተመሰረቱ ናቸው እና ስለዚህ በቀን አንዳንድ ልዩነቶች ሊሆኑ ይችላሉ*
*በፆም ምክንያት የተማሪ ተከታዮች ፍላጎቶቻችን ለማስተናገድ(ለማመቻቸት) በሚከተሉት ሁሉም ቀናት እና ከቀኑ(ኖች) በፊት ባሉት ምሽቶች ንቁ ይሁኑ።እነዚህ ቀኖች ድመቀው ተዘርዝረዋል።*

የሚከተለው መረጃ የዋሽንግተን ስቴት የህዝብ ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ ነው፥

https://ospi.k12.wa.us/policy-funding/equity-and-civil-rights/information-families-civil-rights-washington-schools/religion-schools/common-religious-and-us-public-holiday-calendars

## የ2023-2024 የትምህርት ዘመን ሃይማኖታዊ እና ህዝባዊ በዓላት

**ማስታወሻ:**
**ሁሉም የ Jewish እና የ Islamic በዓላት የሚጀምረው ከበዓሉ የመጀመሪያው በቀን በፊት ያለው ምሽት ፀሐይ ስትጠልቅ ነው።**
*** እነዚህ በዓላት (ወይም በበዓላቶች ውስጥ ያሉ ቀናቶች) የማይሰሩ (የሚከበሩ) ቀናት ተብለው የተሰየሙ ናቸው።**
**# ከእነዚህ ቀናቶች ውስጥ የተወሰኑት በቀን መቁጠሪያ ላይ የተቀመጡ አይደሉም ነገር ግን በጨረቃ እይታ ላይ የተመሰረቱ ናቸው ስለዚህም በቀን አንዳንድ ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ።**

**ሰኔ 28-29, 2023** (ረቡዕ-ሐሙስ) ፣ Eid-al-Adha፣ Islamic
**ሀምሌ 19, 2023** (ረቡዕ)፣የMuharram የመጀመሪያ ቀን (Al Hijrah አዲስ አመት) ፣Islamic፣ Muharram በእስልምና አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው ። የMuharram የመጀመሪያ ቀን በብዙ ሙስሊሞች ዘንድ እንደ የእስልምና እምነት የአዲስ አመት መጀመሪያ ይቆጠራል።
**መስከረም 4, 2023** (ሰኞ)፣ የሰራተኞች ቀን፣ትምህርት የለም
**መስከረም 6-7, 2023** (ረቡዕ-ሐሙስ) ፣ Janmashtami, Hindu
**መስከረም 15-17, 2023** (አርብ-እሁድ) ፣ *Rosh Hashanah (አዲስ አመት) ፣ Jewish፣ Rosh Hashanah kicks off several weeks of Jewish holidays in the fall. Rosh Hashanah እና Yom Kippur የተቀደሱ ቀናት ተብለው የሚጠሩት ሁለቱ በጣም የተከበሩ የJewish በዓላት ናቸው።
ለተከታዮች የስራ ቀን ያልሆነ።
**መስከረም 24-25, 2023** (እሑድ-ሰኞ) ፣ *Yom Kippur (የስርየት ቀን) ፣ Jewish፣ የተቀደሰ እና በጣም የተከበረ የ Jewish በዓል።
ለተከታዮች የስራ ቀን ያልሆነ።
**መስከረም 26-27, 2023** (ማክሰኞ-ረቡዕ), Mawlid-al-Nabi (የመሐመድ የልደት ቀን) ፣ Islamic
**መስከረም 29- ጥቅምት 6, 2023** (ዓርብ-አርብ) ፣ *Sukkot (Feast of Tabernacles) ፣ Jewish፣ ለተከታዮች የስራ ቀን ያልሆነ።
**ጥቅምት 6-8, 2023** (አርብ-እሁድ) ፣ *Shmini Atzeret፣ Jewish፣ ለተከታዮች የስራ ቀን ያልሆነ።
**ጥቅምት 7-8, 2023** (ቅዳሜ-እሁድ) ፣ *Simchat Torah ፣ Jewish፣ ለተከታዮች የስራ ቀን ያልሆነ
**ጥቅምት 9, 2023** (ሰኞ)፣ የአገሬው ተወላጆች ቀን
**ጥቅምት 15-23, 2023** (ከሰኞ በኋላ የእሁድ-ሰምንት) ፣ Navaratri/Dassehra ፣ Hindu፣ በሌሊት ይከበራል።
**ህዳር 11, 2023** (ቅዳሜ)፣ የአርበኞች ቀን፣ህዳር 10,2023 (አርብ) ትምህርት የለም
**ህዳር 12, 2023** (እሁድ)፣ Diwali, Hindu
**ህዳር 23, 2023** (ሐሙስ)፣ የምስጋና ቀን፣ከህዳር 23-24፣ 2023 (ሐሙስ-አርብ) ትምህርት የለም
**ታህሳስ 7-15, 2023** (ሐሙስ-አርብ) ፣ Hanukkah (Chanukah)፣ Jewish
**ታህሳስ 25, 2023** (ሰኞ), የገና ቀን፣ ክርስቲያን፣ ትምህርት የለም
**ጥር 1, 2023** (ሰኞ)፣ የአዲስ ዓመት ቀን፣ ትምህርት የለም
**ጥር 7-8, 2024** (እሑድ-ሰኞ) ፣ የኦርቶዶክስ ገና፣ ክርስቲያን ኦርቶዶክስ
**ጥር 15, 2024** (ሰኞ)፣ የማርቲን ሉተር ኪንግ ቀን፣ ትምህርት የለም
**የካቲት 10, 2024** (ቅዳሜ)፣ የጨረቃ አዲስ ዓመት
**የካቲት 14, 2024** (ረቡዕ)፣ Ash Wednesday ፣ ክርስቲያን
**የካቲት 14, 2024** (Wed)፣ የዐብይ ጾም መጀመሪያ ፣ Christian፣ ከየካቲት 14 እስከ መጋቢት28፣ 2024 ይከበራል
**የካቲት 19, 2024** (ሰኞ)፣ የፕሬዚዳንት ቀን፣ ትምህርት የለም
**መጋቢት 8, 2024** (ዓርብ)፣ Maha Shivaratri፣ Hindu

Amharic

**መጋቢት 10, 2024** (እሁድ), የረመዳን መጀመሪያ፣ከመጋቢት 10 እስከ ሚያዚያ 10፣2024 ይከበራል።
**መጋቢት 23-24, 2024** (ቅዳሜ-እሁድ) ፣Purim፣Jewish
**መጋቢት 25, 2024** (ሰኞ)፣Holi፣ Hindu
**መጋቢት 29, 2024** (ዓርብ)፣አርብ ስቅለት፣የክርስቲያን
**መጋቢት 31, 2024** (እሁድ)፣ፋሲካ፣ ክርስቲያን
**ሚያዚያ 6, 2024** (እሁድ)፣Lailat Ul Qadr, Islamic፣ቀን አልተወሰነም፣ከላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ
**ሚያዚያ 10, 2024** (ረቡዕ)፣Eid al-Fitr (የረመዳን መጨረሻ) ፣Islamic፣ከመጋቢት 10 እስከ ሚያዚያ 10፣2024 ይከበራል
**ሚያዚያ 17, 2024** (ረቡዕ) ፣Ram Navami፣ Hindu
**ሚያዚያ 22-30, 2024** (ከማክሰኞ በኋላ የሰኞ-ሰምንት) ፣Jewish፣ከሚያዚያ 23-24 እና ከሚያዚያ 29-30 ሥራ አይፈቀድም።ከሚያዚያ 25-26 እና ከሚያዚያ 28 ከገደቦች ጋር ሥራ ይፈቀዳል።
**ግንቦት 3, 2024** (ዓርብ)፣የኦርቶዶክስ አርብ ስቅለት፣የክርስቲያን ኦርቶዶክስ
**ግንቦት 5, 2024** (እሁድ)፣የኦርቶዶክስ ፋሲካ፣ክርስቲያን ኦርቶዶክስ
**ግንቦት 27, 2024** (ሰኞ)፣የመታሰቢያ ቀን፣ትምህርት የለም
**ሰኔ 11-13, 2024** (ማክሰኞ-ሐሙስ) ፣*Shavuot፣Jewish፣ለተከታዮች የስራ ቀን ያልሆነ
**ሰኔ 16-17, 2024** (እሑድ-ሰኞ) ፣Eid al-Adha, Islamic፣ቀን አልተወሰነም።ከላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ።
**ሀምሌ 4, 2024** (ሐሙስ)፣የነጻነት ቀን፣ትምህርት የለም
**ነሐሴ 26, 2024** (ሰኞ)፣Janmashtami፣Hindu፣ቀን አልተወሰነም፣ከላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ።